የኢትዮጵያውያን ሕዝባዊ ማህበራት ጉባኤ (ኢሕማጉ)
Congress of Ethiopian Civic Associations (CECA

ኢሕማጉ (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ማኅበራት ጉባኤ) የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግሬስ
በአማራ ወገኖቻችን ላይ የሕዝብ ለሕዝብ የጥላቻ ቅስቀሳን በፅኑ ያወግዛል
July 12, 2024

## ጋዜጣዊ መግለጫ

ከአስራ አምስት ዓመታት በፊት በዘር ፖለቲካ ላይ ቢመሰረትም የዲሞክራሲ ሥርዓት አራማጅ ተብሎ የተቋቋመው የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) እነሆ አሁን ለይቶለት የዘረኛ ጨፍጫፊዎች የብልጽግና መንግሥት ተብዬውና የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን ጠበቃ ሆኖ ብቅ ብሏል። መሪዎቹ (ዶ/ር መራራ ጉዲና፤ አቶ ጃዋር መሀመድና አቶ በቀለ ገርባን ጨምሮ) ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ሰው በሰው ላይ የማነሳሳት በተለይም በኦሮምያ ክልል ውስጥ በሚገኙ አማሮች ላይ ከፍተኛ የጥፋትና የእልቂት የቅስቀሳ ዘመቻዎችን ሲያደርጉ ከርመዋል።

ኢሕማጉ የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግሬስ በኦሮሚያ ክልል በሚኖሩ ሁለተኛ ዜጋ በሚላቸው አማራዎች ላይ ያወጀውን የጅምላ መቀጣጫ ፍረጃ በማያወላዳ መንገድ እንቃወመዋለን፤ በከፍተኛ ድምፅም እናወግዘዋለን። በዚህ ድርጊቱም የሰው ልጅን መሠረታዊ የመኖርና ሰብዓዊ መብትን በመካድ ከሌሎች ጽንፈኛ ድርጅቶች ጋር በማበር የጅምላ ጭፍጨፋን ሲቀሰቅስ እስካሁን ይታያል። አማራውን ነፍጠኛ፤ ቅኝ ገዢ፤ ሰፋሪ ብሎ ካላግባብ በመፈረጅና በኬኛ ፖለቲካ አባዜ ተጠምዶ ክልሉን በጉልበት በማስፋትና አዲስ አበባን ጠቅልሎ በመያዝ በበላይነት የመግዛት ሲያሻው ደግሞ በተጨቋኝነት ትርክት ራሱን እያንኳሰሰ ከተሳካለት ግን ለመገንጠል የሚገፋውን እብሪተኛ አጀንዳ እያራመደ ይገኛል።

ኦፌኮ ለስልጣን ፉክቻ ቅድሚያ ሰጥቶ የዐብይ መንግስትን ለመገዳደር ሲፈልግ የኦሮሞ ሕዝብን ስለማይታደግ ሕዝቡ እራሱን እንዲያስታጥቅ ጥሪ ያቀርባል፤ ሲፈልግ ደግሞ አማራው ታጥቆ ወደ ህልውና ትግል ሲገባ ስጋታችን ነውና ሃይ ይባል ብሎ ለመንግስት አቤቱታ ሲያቀርብ ይስተዋላል ። በተለይም በኦሮሚያ ክልል በአማራ ላይ የተደረገውን ጭፍጨፋ መካድና አማራ መጣብህ ብሎ በውሸት የኦሮሞ ሕዝብን ለእርስ በርስ ጦርነት የመቀስቀስ ወንጀልና ለዘር ማፅዳትና ማጥፋት ወንጀሎች ቅድመ-ሁኔታዎችን እንዲፈጠሩ ማስቻል፤ ስለሆነ በዩጎዝላቪያ፤ ሚያንማርና ሩዋንዳ እልቂቶች ጋር ተነጻጻሪ ነው።

ለማስረጃ ያህል እ.ኤ አቆጣጠር ዲሴምበር 8/20/22 ኦፌኮ በእንግሊዝኛ ያወጣውን ጋዜጣዊ መግለጫ እንመልከት፤

> “ከቅርብ ጎረቤት የተነሣው አማራ ፋኖ (በተለየ በጨካኝ ተግባሩ የሚታወቀው በ2020-2022 የትግራይ ጦርነት ጊዜ በፈጸመው የህዝብ ጭፍጨፋ የሚታወቀው) እንዲሁም በተለያዩ የአማራ ባለድርሻ ነን ባይ አካላት የተደገፈ የክልል ሚሊሺያ ወደ ኦሮሚያ እየገባ ነው ... ከገቡም በኋላ በወጣት ኦሮሞዎች ሬሳ ላይ ኢሰብዓዊ ድርጊቶችን ፈጽመዋል” ይላል።

ይህ ገለጻ ፈጽሞ ከእውነት የራቀና የፈጠራ ወሬ ነው። በመሠረቱ የአማራ ፋኖ እንደ ንቅናቄ የተቋቋመው፤ የተጠቀሰው የኦፌኮ መግለጫ ከወጣ በኋላ እንደ ኢ.ኤ. አቆጣጠር በ 2023 መሃል ላይ ነው። በትግራይ ጦርነት የአማራ ፋኖም ሆነ ሚሊሺያ እራሱን በራያና ወልቃይት ገድቦ እየተከላከለ የነበረ ሃይል ነበር። መንግስት የዳቦ ስም ሰጥቶ ካደራጃቸው ነፍሰገዳዮች በቀር ፋኖም ሆነ የአማራ ሚሊሺያ ፈጽሞ ወደ ኦሮሚያ ገብቶ አያውቅም። ይህ የፈጠራ ወሬ ሆን ተብሎ በወለጋ ኦሮሚያ ክልል በግፍ በየጊዜው ዓለም በሚያውቀው ሁኔታ በበቂ ማስረጃ የተወገዘውን የዘር ፍጅት አሁንም ድረስ አማሮች ላይ እየተፈፀመ ያለውን ዘግናኝ ዕልቂት ለመሸፈን መሆኑ ግልጽ ነው። ‘የአብዬን ወደ እምዬ ይሉሀል ይህ ነው’። የኢትዮጵያ ስብዓዊ መብት ኮሚሽንም በወቅቱ በሚገባ ቢመዘግበውም ኦፌኮ እያወቀ ከመጥቀስ ተቆጥቧል።

የኦሮሞ ፌደራል ኮንግሬስ ፋኖ እንዲደመሰስ ያላባራ ጥሪና ዘመቻ በማድረግ ላይ ተወጥሯል። ከ2023 መጀመሪያ ጀምሮ ፋኖ ለኦሮምያ ክልልና የፌደራል መንግሥቱ ትልቅ አደጋ በመሆኑ ትጥቁ ተፈቶ በሀይል መመታት እንዳለበት የብልጽግናን መንግስትና የኢትዮጵያ ብሄራዊ መከላከያ ሠራዊትን በተደጋጋሚ አሳስቧል። ለፋኖ 'ፅንፈኛ' የሚለውን ቅፅል ስምም ያወጣለት እሱ ነው።

በቅርቡም ካለምንም ማስረጃ ፋኖ በምዕራብ ሸዋ ናኖ በሚባል ቀበሌ ሰርገኞች ላይ ፋኖ ጥቃት አድርሷል የሚል መሠረተ ቢስ ክስ ሰንዝሯል። እ.ኤ አቆጣጠር ሰኔ 25 ቀን 2024 ዓም ኦፌኮ በፌስቡክ ገጹ ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ አማራን ከኦሮምያ ክልል በሙሃሪያ ሀይል የማጽዳት እርምጃ በሰፊው እንዲወስድ እንደሚከተለው ጥሪ አቅርቧል፡-

> "እነዚህ ጽንፈኛ ታጣቂዎች በተለያየ ጊዜ በወለጋ የተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች ነዋሪዎች ላይ ተመሳሳይ ጥቃቶችን ሲያደርሱ እንደነበሩና እንደዚያም እንዲያደርጉ የልብ ልብ የሰጣቸው ደግሞ በሰሜኑ ጦርነት ወቅት እስከ አፍንጫቸው የታጠቁት የጦር መሣሪያና ያገኙት ሎጂስቲክስ እገዛ እንደሆነ ይታወቃል...በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ተጠቁ በሚል ትርክት መታጠቅ እንዳለባቸው በሚል ሰበብ ባለፉት አመታት በመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጭምር መታጠቅ እንዳለባቸው ሲነገር መቆየቱም ይታወቃል.... በኦሮምያ ክልል የአማራ ተወላጆችም በስሙ ተደራጅተው ንጹሀን ላይ ጥቃት የሚያደርሱ ጽንፈኛ መሸሸጊያ እንዳይሆኑ አጥብቀን እንመክራለን።"

ይህን ሲል ኦፌኮ አይኑን ጨፍኖ የሚከተሉትን ግናዛቤዎች አራምዷል፡- 1) የፋኖ ጽንፈኛ ሀይሎች ኦሮሚያን በስፋት እያጠቁ ነው፤ 2) የውጊያ ሀይላቸውን የገነቡት በሰሜኑ የትግራይ ጦርነት ወቅት ነው፤ 3) በኦሮሚያ ክልል የሚኖሩ አማራዎች በዘር ተጠቅተዋል በሚል የውሸት ትርክት በሚያሰጋ መንገድ በፍኖነት እየታጠቁ ነው፤4) በኦሮሚያ የምትኖሩ አማራዎች ለፋኖዎች መጠለያ እንዳትሰጡ እጥብቀን እናስጠነቅቃለን የሚሉ እኩይ መልዕክቶች ናቸው።

የኦሮሚያ ነዋሪዎችን በመንግሥት ከተቀነባበረ ጥቃት ኦፌኮ የሚያደርገውን ማጋለጥ የምንደግፈው ቢሆንም፤ በአማራው ላይ የሚደርሰውን ጭፍጨፋ መፈናቀልና እንግልት በእኩይ መንፈስ እየመረጠ በተደጋጋሚ የሚፈፅመው ክህደት ይቅርታ የማይደረግለት ታሪካዊ ስህተት ነው። በዚያውም መጠን ለዘረኛው ገዢ ፓርቲና በማፊያነት ለተሰማራው የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት እውቅናና ደጋፍ መቸር ነው። ለሰው ልጅ እኩልነት ፤ አንድነትና ፍትህ የቆሙ ኢትዮጵያውያኖች ሁሉ የኦፌኮን ማስረጃ አልባ ፍረጃ ሊያወግዙት የሚገባ የሀገር ጉዳይ ነው።

ኢሕማን፤ ኦፌኮ በመዝቀጥ የፖለቲካ ፅንፈኛነትንና ነውጠኛነትን መደገፉ እጅግ አሳዝኖናል። ደጋግሞ ያቀረባቸው መርዘኛ መግለጫዎችና መርህ አልባ ምልከታ ከዴሞክራሲ የራቀና፣ አግላይነትን ያቀፈ በመሆኑ ለኢትዮጵያ አንድነትም ሆነ ለኦሮሞ ሕዝብ ጥቅምና ክብር አይመጥንም። በዚህ የዘረኝነት ቁልቁለት ላይ ያለው ኦፌኮ በአሁኑ ወቅት በሚካሄደው ዜጋ-ተኮር ሀገር አቀፍ ሀገመንግሥታዊ የሽግግር እንቅስቃሴ ውስጥ አስተማማኝ የፓለቲካ አጋር ለመሆን እንደማይችልም ተገንዝበናል።

ድል ለአማራ ሕዝባዊ የህልውና ንቅናቄ፣
ኢትዮጵያችን በጀግኖች ልጆችዋ እንደቀድሞው ነጻነትዋን ያለጥርጥር በአሸናፊነት ትጎናጸፋለች!